# ኢትዮጵያዊቷ ማንዴላ ከእስር ቤት ትወለዳለች

በቃሊቲ እስር ቤት የምትገኘው ወጣቷ የህግና የፖለቲካ ሰው ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳን ከእናቷና ከልጇ በስተቀር ሌላ ጠያቂ እንዲያያት አይፈቀደም የሚል ዜና ብሰማም ወደ ቃሊቲ ከመሄድ አላገደኝም። ለዚህም ምክንያቴ ሁለት ነበር። አንደኛው በህገ-መንግስቱ ላይ በግልፅ የሰፈረ በወዳጅ በዘመድ የመጠየቅ መብት በወህኑ ቤት አላፊዎች ስለመጣሱ በቦታው ተገኝቼ በአይኔ ተመልክቼ አማኝ ለመሆን ሲሆን ሁለተኛው አግኝቼ እንዴት ነሽ ልላት ባልችልም ቢያንስ ቦታው ደርሼ መመለስ ለህሊናዬ ትንሽ እፎይታ የሚሰጠኝ ሆኖ ስልተሰማኝ ነው።

ቃሊቲ ስደርስ እናቷን በር ላይ እየተንጎራደዱ ግቡ እስኪባሉ ሲጠብቁ አገኘኋቸው። ቀደም ሲል በደንብ አላውቃቸውም ነበር እና ትልቅ ሴት መሆናቸውን ያወኩት ያኔ ነው። እንቦቀቅላ ልጇ ሀሌም ከአክስቷና የብርቱካን ሹፌር እንደሆነ የተነገረኝ ወጣት ጋር ትጫወታለች። አክስቷ የምትሄደው ለሀሌ ለህፃኗ ብላ እንጂ ብርቱካንን እህቷን የመጠየቅ ዕድል እንደተነፈገች ተነገረኝ እዛው ቆይቼም አረጋገጥኩ።

አስገራሚው ገጠመኝ ደግሞ ሀሌ ከአያቷ ጋር እንድትገባ ቢፈቀድላትም አክስቷ ካልገባች አልገባም ስትል እኔን አያስገቡኝም አንቺ ከእማዬ ጋር ግቢ ስትላት ህፃኗ የተናገረችው ነይ እንግባ ይቅርታ እንጠይቃቸዋለን “ይቅርታ ጠይቂ አይደል ያሏት” ነበር ያለቸው ህፃን ሀሌ። አነጋገሯ በቦታው የነበሩትን በሙሉ የንዴትና የቁጭት ፈገግታ ያሰፈገገ ነበር። የአክስቷ ክልከላ ሊነሳ ባለመቻሉ እንደምንም አባብለን ህፃኗን አስገባናት። ሰዎቹ ይህንን በማድረጋቸው ሊያገኙ የሚችሉት ጥቅም ግን ባስበው ሊገባኝ አልቻለም።

ብርቱካንን ከማውቃት በላይ መሆኗን ራሴን ጠይቄ የተረዳሁት አሮጊቷ እናቷንና ህፃን ልጇን ካየሁ በኋላ ነው። በብርቱካን ቦታ እራሴን አስቀምጬ እሷ የፈፀመችውን ቆራጥነት እና ድፍረት የምፈጽመው ስለመሆኑ ፈተንኩት እርግጠኛ ሆኜ መልስ ልሰጥ ግን አልቻልኩም።

ብርቱካን የተማረችው የህግ ሙያ ጥቁሩን ካባ ለብሳ እጇን ከፍ አድርጋ የገባችው መሀላ እንደቀላል ሌሎቹ ሲያደርጉት እንደምናየው ልታልፈው እሚቻላት አልሆነም። ትናንት በቅንጅት ዛሬ ደግሞ በአንድነት ለመሪነት ስትመረጥ ቅዱሱን መፅሃፍ አስይዞ ቃለ መሃላ ያስገባት ባይኖርም እሷ ለራሷ የገባችውን ቃል እንደሌሎቹ ፖለቲከኞች ጎመን በጤና ብላ ለአፍታ እንኳን ልትሽረው ህሊናዋ አልፈቀደላትም። ቃል የዕምነት ዕዳ ሆነባት። ሞራል በፖለቲካ ተውጦ እውነት በማስመሰል ክህደት ተረግጦ፤ ውሸት የፖለቲካ ስራው አንድ ስልት ሆኖ በምንኖርበት ሃገር “ውሸት ለመናገር አትችም ምላሴ ለእውነት እሰዋለሁ አልሳሳም ለነብሴ” ብላ ወህኒ መውረድ መረጠች። በዚህ አጋጣሚ ይህን ተግባሯን በሚገባ የሚገልፀውን የአርቲስት ጥላሁን ገሠሠን ዘፈን ለጀግንነቷ መታሰቢያ ይሆን ዘንድ መርጬላታለሁ።

የመስቀሉ ስር ቁማርተኞች በሚል ርዕስ እውነትን ደፍሮ የፃፈው ዲያቆን በጋሻው በዚሁ መፅሀፉ ውስጥ “ለእውነት ስትቆም፤ ለህሊናህ ስትታመን አለም በአንተ ላይ መዝገብ ሙሉ ክስ አላት፤ አላማዋም አንተን መወንጀል እና በጉስቁልና መቅሰፍት መምታት ብቻ ይሆናል” ይላል። በወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ ላይ አንቀጽ የማይጠቀስበት፤ ማስረጃ የማይቀርብበት፤ እንዲ ብል ይሻል የሚል ክስ መስርተው ለቃሊቲ እስር የዳረጓት ለዕውነት በመቆሟ ለህሊናዋ በመታመኗ ብቻ ነው። አሳሪዎቿ ግን የዚህ አይነት ብቃት እንደሌላቸው ከመጀመሪያው ድፍረታቸው እና በሁለተኛው ሥራቸው አረጋግጠዋል። ወዳጅ ዘመድ እንዳይጠይቃት መከልከል ያውም ሕገ-መንግስትን ጥሶ ህሊና ቢስነት ነው።

የቅንጅት ታሳሪዎችን በይቅርታ ስለማስፈታታቸው በመንግስት የመገናኛ አውታሮች ሲነግሩን የከረሙት ፕ/ሮ ኤፍሬም ይስሀቅ እና አብረዋቸው የነበሩ በርካታ ሽማግሌዎች ናቸው። እኛም ጉዳዩን በቅርብ ስንከታተል የነበርን ሰዎች ይህን ለማወቅ ነጋሪ የሚሻን አይደለንም። ይህን አገር ያወቀው ፀሀይ የሞቀውን ሃቅ ነው ወ/ት ብርቱካን የተናገረችው። እሷ ስለተናገረችው ብቻ ወንጀል የሚሆንበት የህግ አግባብ አይታየኝም። የመንግስትም መግለጫ ይህንን ማሳየት አልተቻለውም።

ህግን የገዢ ፓርቲ አላማ ማስፈፀሚያ አድርገው የሚጠቀሙበት ወገኖች ለዝንት ዓለም በስልጣን ላይ እንደሚቆዮ እያሰቡ ከሆነ በእርግጥም ስልጣን ያሳውራል። ዛሬ እነሱ በተቀመጡበት ወንበር ላይ ከነበሩት የትናንት ባለስልጣናት መሀከል አብዛኞቹ ዛሬ ቃሊቲ እንደሚገኙ ረስተውት ይሆን?

ብርቱካን የመጨረሻውን ውሳኔ ስትወስን በአንድ በኩል ከነበርሽበት እስር ቤት እንመልስሻለን የዕድሜ ልክ ቅጣቱም ተፈፃሚ ይሆናል የሚለው የፖሊስ ማስፈራሪያ፣ በሌላ በኩል ለ21 ወራት በእሷ መታሰር ሲሰቃዩ ሲቸገሩ ከርመው ገና በወጉ እፎይ ያላሉት አሮጊት እናቷን ገና ያልጠገበቻት ህፃን ልጇ እንዲሁም በሊቀ-መንበርነት የምትመራው ፓርቲ ቀጣይ ህልውና መንፈሷን እየተፈታተኗት የነበሩ ስለመሆናቸው መገመት አይገድም። በዚህ ውስጥ ሆኖ እሷ የወሰደችውን የመጨረሻውና ከባዱ ውሳኔ ላይ መድረስ ቆራጥ መሆንን ይጠይቃል። ይህ ብዙዎቻችንን ልንጋፈጠው የማንችለው ግን ደግሞ ትክክለኛ ውሳኔ ነው።

ብርቱካን በዚህ ሂደት ውስጥ ሶስት ምርጫዎች ነበሯት። የመጀመሪያው የማስፈራሪያው ወሬ ሲበዛ እዛው አውሮፓ መቅረት፣ ሁለተኛው የተባለችውን ፈጽማ ተንበርክካ መኖር፤ ሦስተኛው ለቃሏና ለእውነቱ አምና፣ በዕምነቷ ፀንታና የሞራል የበላይነቷን ጠብቃ የሚመጣውን ሁሉ በፀጋ መቀበል። የመጀመሪያ ሁለቱ ለወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ እንደምርጫም የሚቀርቡ አይደሉም። እናም ቅሌትን ድል ነስታ፣ ከነክብሯ ወደ ቃሊቲ ወረደች። ራሷን አከበረች፣ በሰዎች ተከበረች፣ የአሳሪዎችንም ምንነት በገሀድ አሳየች።

ቀኑ ሲደርስ አይቀሬ የሆነውን ሞት በመፍራት ብዙዎቻችን ራሳችንን እናቀላለን፣ ቃላችንን እናጥፋለን፣ እምነት እናጎድላለን፣ እንዋሻለን፣ ጎመን በጤና ብለን ለመንደር አምባገነኖች ሳይቀር እናጎበድዳለን፣ ይህነን ካደረግን በኋላ ግን መንፈሳችን ሞቶ የሚኖረው በድናችን/ሥጋችን ብቻ መሆኑን አስበነው እምናውቅ ስንቶቻችን እንሆን?

በሊብራል አቋሙ የሞታወቀው አሜሪካዊው ሄነሪ ዲቨሮቶ "እንደ ሙብቴ የምቆጥረው ብቸኛ ግዴታዬ ትክክለኛ የመሰለኝን ሁሉ መሥራት ነው" ይል ነበር። ይሄው ሰው በ 1949 ዓ.ም. አሜሪካን ውስጥ የነበረውን የባሪያ ንግድ ሥርአትን እና የሞክሲኮ ወረራን በመቃወም ይጽፍ ነበር። ታዲያ በዚሁ ተቃውሞው ምክንያት ታጣቂዎች እያዳፉ ወደ ወህኒ ቤት ሲወስዱት "ወደ እስር የሚወስደው ትክክለኛው መንገድ በህዝብና በሃይማኖት ስም ወደ እስር ቤት ሄዶ መሰቃየትና የብቸኝነትን ፅዋ መቅመስ ነው"። የእስረኛው ነብስ ነፃ መሆኑን በዚህ ሁኔታ ሊረዳው መቻል አለበት። እኔ ይህ ደስታ ተሰምቶኛል፣ ለአንዲት ሰከንድ እንኳን ከህዝብ የተገለልኩ መሆኔ እልተሰማኝም። ከቶውንም ልግድዳዎቹ መስሪያ የዋለው ድንጋይ እና ሲሚንቶ መባከን ይሰማኛል። ማለቱ ይጠቀሳል።

ለአንዲት ወ/ት ብርቱካን በአራት መኪና ከ10 በላይ የሚሆኑ ታጣቂዎች መጥተው ሲከቧት፣ ሲያንገላቷት እና እየተሳደቡ ወደ ወህኒ ቤት ሲወስዷት ምን እንደተሰማት ለማወቅ አጋጣሚው ባይኖረንም የሄነሪ አይነት ስሜት ሊኖራት እንደሚችል ግን መገመት አይገድም።

ሄነሪ የእስረኛው ነብስ ነፃ ነው እነዳለው የብርቱካን ነብስ ነፃ ስለመሆኑ ጥርጥር አይኖረኝም። ነፃነት የማይሰማቸው እና በዚህ ሁኔታ እስካሉ መቼም ሊሰማቸው የማይችለው አሳሪዎቿ ግን ለብቻዋ በማሰር አና ጠያቂ በመከልከል ነፃነት የለሾች መሆናቸውን አስምስከሩ። ነፃነት ያለው ቀርቶ እነዲኖረው የሚመኝ እና እነደሚገባውም የሚያምን ሰው የሌላውን ነፃነት አይጋፋም። መፅሃፉም በራስህ እንዲሆን የማትፈልገውን በሌላው ላይ አታድርግ ነው የሚለው። እነዚህ ሰዎች ግን ነፃነትም ያለቸው አይመስለኝም።

ለምድራዊው ህግ የሚገዙ አይደሉም እነሱ ሕገ-መንግስት ይጥሳሉ። አምላካዊውን ትዕዛዝ አያከብሩምና አታድርጉ የተባለውን ያደርጋሉ። ሠዋዊ ባህሪ ይጎድላቸዋል እንዲሁም ነግ በእኔ አያውቁም። ለዝንት ዓለም በስልጣን ላይ የሚኖሩ ይመስላቸዋል። የሥልጣናቸው ነገር እያስጨነቃቸውም ለራሳቸው ነፃነት አጥተው ሌላውን ነፃነት ለማሳጣት ይጥራሉ።

ሰዎችን ለይተው ለብቻ በጨለማ ቤት በማሰርና ጠያቂ በመከልከል ህገ-ወጥ ድርጊት ይፈፅማሉ። በዚህም ነፃነቱን የቀሙት ቂማቸውን የተወጡበት መስሎ ይሰማቸዋል። በተግባር ግን ነፃነታቸውን ያጡትና እየተሸነፉ ያሉት እነሱ ናቸው። ይህ ድርጊታቸው የታሳሪውን የሞራል የበላይነት ይበልጥ የሚያረጋግጥና የእነርሱን ፈሪነት የሚያሳብቅ ነው።

ውሻ አንድን ሰው አባሮ ሲይዘው ከወደቀ ቆሞ ያየዋል አልያም ጥሎት ይሄዳል እንጂ በወደቀበት አይነክሰውም። በእጅ ካስገቡ ወይም በቁጥጥር ስር ካዋሉ በኋላ ምንም መላወሻ በሌለው ሰው ላይ በደል መፈፀም ጅብ የነከሰች አህያን መሆን ነው። ይህ ደግሞ በሥነ-ምግባር ደረጃ ከውሻውም ማነስ ነው።

በብርቱካን ላይ የተፈፀመው ህገ-ወጥ ተግባር ሁሉ የብርቱካንን እውነተኛነት የሚመሰክር እና የሞራል የበላይነት የሚያጎናፅፋት ሲሆን በአንፃሩ ደግሞ እነዴት ተደፈርን በሚል ስሜት የተሸናፊነት ተግባር እየፈፀሙ ያሉ መሆኑን አሳሪዎቹ አጢነውት ይሆን?

ሰውን ማሰር እረ እንዳውም መግደል ሁሉ ይቻል ይሆናል፤ ስንቶች ሞተዋል። ልቡን ማሰር፤ ዓላማና ዕምነቱን መግደል ግን በፍፁም አይቻልም። ማንዴላ 27 ዓመት ሲታሰር (ጀግና አንቱ አይባልም) ዓላማው ታስሮ አልቀረም። ማርቲን ሉተር ኪንግ ሲገደል ህልሙ አብሮት አልሞተም። ኢትዮጵያዊቷም ማንዴላም ከእስር ቤት ትወለዳለች።

ከአንድነት ወጣት አ/አ